

## የእፅዋት ጤናና ምርት ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት/ *Plant health and product quality control directorate*

ዳይሬክቶሬቱ ለእፅዋት ኳራንታይን፤ ለፀረ ተባይና ማዳበሪያ ጥራት ቁጥጥር የሚረዱ የህግ ማአቀፎችን ከሚኖረው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ወቅታዊ ያደርጋል፣ መተግበራቸውን ይከታተላል፤ ከሚመለከተው ጋር በመሆን ክልላዊ የእፅዋት ኳራንቲን (Regional Quarantine) ስርዓት በክልሉ እንዲተገበር ያደርጋል፤ አስፈላጊ መግቢያና መውጫ በሮች ላይ የቁጥጥር ጣቢያዎች እንዲከፈቱ ያደርጋል፤ ያደራጃል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤ ከብሄራዊ የእፅዋት ኳራንቲን ሰርዓት ጋር በቅንጅት የሚሰራበትን መንገድ ያመቻቻል፣ ያስተባብራል፤ መረጃዎችንም ይለዋወጣል:: ዳይሬክቶሬቱ ወደ ክልል ውስጥ የሚገባ ዕፅዋት፣ ዕፅዋት ውጤቶችና ማንኛውም ቁጥጥር የሚደረግባቸው ቁሳቁሶች በደንብና መመሪያ የተቀመጡትን መስፈርቶች አሟልተው መሆኑን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣ የእፅዋት ኳራንቲን ተባይ ይዘው መገኘታቸው በምርመራ ከተረጋገጠ የማከም፣ የማስወገድ ወይም ወደ መጣበት ክልል የመመለስ እርምጃ እንዲወሰድ ውሳኔ ይሰጣል። በመሆኑም እርምጃ አወሳሰዱን በተመለከተ የፋይቶሳኒተሪ እርምጃ ማሳወቂያን በተከተለ መልኩ ለላኪው ክልል ወይም አካል ይልካል፣ ለአፈጻጸሙ በተላከው ግብረ መልስም መሰረት ክትትል ያደርጋል፤ ለሚቀርቡ ቅሬታዎችና መረጃዎች ወቅታዊ ምላሽ ይሰጣል። በክልሉ በየጊዜው ተከታታይ የተባይ ቅኝትና አሰሳ በማካሄድ በመስኩ ከተገኙት ምርምር ዉጤቶች መረጃ በመነሳት ስለ አዳዲስ የተባይ ክስተቶች ለብሄራዊ ዕፅዋት ጥበቃ መረጃዎችን ያስተላልፋል፤ ከመስፋፋታቸው በፊት በእርምጃ አወሳሰዱ ላይ ይወያያል፤ የክልሉን ፋይቶ ሰኒተሪ አገልግሎት አሰራርና ደረጃን ለማሻሻልና ለማጠናከር የሚረዱ ፕሮጀክቶችን ይቀርጻል፣ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ አስፈላጊ በሆኑ መደበኛ ብሄራዊና ክልላዊ ኮንፈረንሶች ላይ በመገኘት የፋይቶ ሰኒተሪ ደረጃ አወጣጥ፣ ያለበት ደረጃ እና መሻሻል ያሉባቸው ጉዳዮች ላይ አስፈላጊዉን ክልላዊ ግብዓት ይሰጣል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤ ወደ ክልሉ ውስጥ

በገደብ ለሚገቡ ዕፅዋት፣ ዕፅዋት ዉጤቶች እና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸውን ቁሳቁሶች እንዲለዩ ያደርጋል፣ ተፈቅዶላቸው ለመግባት በሚመጡበት ጊዜ በማቆየት ምርመራ የሚደረግባቸው ድህረ መግባት ኳራንቲን ሥራ ቦታዎችን ያዘጋጃል፤ ያደራጃል፣ በፋይቶ ሳኒታሪ እና በዕፅዋት ምርት አሰራር የሚፈለጉ መስፈርቶች ወይም ስታንዳርዶች መሟላታቸውን ለማረጋገጥ የሰነድ፣ የገቢና ወጪ ምርቶች፣ የመስክ፣ የመጋዘን፣ የማጓጓዣ እና ጥቅም ላይ የዋሉ የእርሻ መሣሪያዎች የኢንስፔክሽን ሥራ እንዲከናወን ያደርጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ ከክልሉ ወደ ሌሎች የሚላኩ ምርቶች ከኳራንቲን ተባይ ክስተት አኳያ የመስፈርት መጓደል ላይ ቅሬታ ካስነሳ በማጥናት፤ በማጣራትና እርምጃ እንዲወሰድ ለብሔራዊ የዕፅዋት ጥበቃ መረጃውን ያስተላልፋል፣ ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ክትትል ያደርጋል; የዕፅዋት ኳራንቲን እና የዕፅዋት ምርት ጥራትን አስመልክቶ ለሕብረተሰቡ በሚደረጉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ያስተባበራል፣ በግንባር ቀደምትነትም ይመራል፤  አስገዳጅ ደረጃ ለወጣላቸው እፅዋትና የግብርና ምርቶች ደረጃዎቹ መተግባራቸውን የአፈጻጸም ስርዓት ይዘረጋል፤ ቁጥጥር ያደርጋል፤ ይከታተላል፤ ይደግፋል፤ ከሚመለከተው አካል ጋር የዕፅዋት ኳራንቲን (Domestic Quarantine)' እና የዕፅዋት ምርት ጥራት ቁጥጥር ስራዎች በቅንጅት የሚሰራበትን መንገድ ያመቻቻል፣ ያስተባብራል፤  ከኳራንታይን ተባይ ነጻ አካባቢዎችን እንዲለዩና እንዲታወቁ ያደርጋል፤ ያጸድቃል፣ የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ክልላዊ አገልግሎት ሊሰጥ የሚችል ማዕከላዊ የልየታ ላቦራቶሪ እንዲቋቋም  አስፈላጊነትን ለሚመለከተው አካል ያቀርባል ተግባራዊነቱንም ይከታተላል።

የአገልግሎት ዘመናቸው ያለፈባቸውን ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ለማስወገድ መረጃ መሰብሰብ፣ ጉዳት እንዳያደርስ ምክረ ሀሳብ መስጠት፣መቆጣጠር፣ ለአወጋገዱም ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ ፀረ ተባይን አስመልክቶ በሚደረጉ ስምምነቶች ክልሉን በመወከል ለመደበኛና ሌሎች ስብሰባዎች ሙያዊ ግብዓቶችን ያበረክታል፤ በማዳበሪያና ፀረ ተባይ ጅምላና ችርቻሮ ንግድና አገልግሎት  በክልሉ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች የሀገሪቱን አዋጅና ደንብ እንዲሁም የክልሉን የአሰራር መመሪያ መሰረት ያደረገ የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፣ በወቅቱ የማደስ ስራ ይሰራል፣ በመስፈርቶች መሰረት አሟልተዉ ለመሥራታቸዉ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል ህግ በሚተላለፉት ላይ የብቃት ማረጋገጫቸው እንዲሰረዝ ያደርጋል አስፈላጊ ሁኖ ሲያገኘውም የፍርድ ውሳኔ እንዲሰጣቸው ለሚመለከታቸው ማስረጃ ያቀርባል፣ ውሳኔውን ይከታተላል፤ በክልሉ ዉስጥ አገልግሎት ላይ እንዲውል የተፈቀደዉን ፀረ ተባይ

ኬሚካል አያያዝ፣ አጠቃቀምና ዝውውር እንቅስቀሴ ይቆጣጠራል፤ በክልሉ ጥራቱ የተጠበቀ ከፍተኛ ምርት ለማምረትና ለሰው፣ ለእንስሰትና ለተፈጥሮ አካባቢ ጎጂነታቸው ዝቅተኛ የሆኑ ፀረተባዮች ለተጠቃሚው በግብዓትነት እንዲውሉ ለማድረግ ይቆጣጠራል፣ ይገመግማል፣ በክልሉ ውስጥ የሚካሄድ ህገ ወጥ የፀረ ተባይና ማዳበሪያ ንግድና ዝውውርን ይከታተላል፤ ህገወጦችን ከሚመለከታቸው የህግ አካላት ጋር በመሆን ለህግ እንዲቀርቡ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤ ከፀረ-ተባይ እና ማዳበሪያ ስራ ጋር በተያያዘ የሚታዩ ቋጠሮዎችን ለመፍታት የሌሎችን ልምድ በመቀመር፣ የመረጃን ወቅታዊነት በማረጋገጥ፤ ከባለድርሻ አካላትጋር በትብብር ስራዎች እንዲሰሩ ሁኔታዎችን ያመቻቻል ፣ይቆጣጠራል፤ የክህሎትና የእውቀት ክፍተቶች ይለያል፤ የአቅም ግንባታና የክህሎት ማሳደጊያ ሥልጠናዎችን ይሰጣል፡፡

**የዳይሬክቶሬቱ አድራሻ**

ባህርዳር ከተማ - ፋሲሎ ክፍለ ከተማ፡ ግብርና ቢሮ ግቢ ውስጥ

**የቢሮ ስልክ ቁጥር** +251582265838

**የዳይሬክቶሬቱ ዳይሬክተር**

**ስም** ሞገስ ዘውዱ አየለ

**ስልክ ቁጥር** 0909525311

ኢሜል moges1852@gmail.com